# መልዕክተ ሰመጉ

ETHIOPIA - EUROPEAN UNION CIVIL SOCIETY FUND II

ሰኔ 2008 ዓ.ም.

በየወሩ የሚወጣ የሰመጉ ልሣን

24ኛ ዓመት ቁጥር 005


## በውስጥ ገፆች


ገጽ 3 ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እና የሥልጣን ገደብ በኢትዮጵያ

ገጽ 6 የኮምፒውተር ዓዋጅ _ ነጻ ሐሳብን የመገደብ ቀጣዩ እርምጃ?

ገጽ 8 ከምርመራ ማኅደር

ገጽ 10 የልማታዊ መንግሥት ዕሳቤ ትግበራ ከሰብዓዊ መብቶች አንፃር

ገጽ 12 ግጥም


# ርዕሰ አንቀጽ

## በሕግ ከለላ ሥር ያሉ ሰዎች ሰብዓዊ መብት ይከበር!

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19፣ 20 እና 21 የተያዙ ሰዎችና የተከሰሱ ሰዎች እንዲሁም በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሠሩ ሰዎች መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡ ፡ በአንቀጽ 19 በተደነገገው መሠረት የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፡፡ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑሥ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የዕምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በአንቀጽ 20 በተደነገገው መሠረት የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ በአንቀጽ 21 በተደነገገው መሠረት በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሠሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡ ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸውና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

ምንም እንኳ የተያዙ፣ የተከሰሱ እንዲሁም በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሠሩ ሰዎች መብቶች በሕገ መንግሥቱ የተከበሩ ቢሆንም በተግባር ግን ከላይ የተጠቀሱት መብቶች በመንግሥት አካላት ሲጣሱ ይስተዋላል፡፡ በተለይም በፖሊቲካዊ ምክንያቶች የታሠሩ ዜጎች ላይ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እጅግ አሳሳቢ ናቸው፡፡ የተያዙ ሰዎች ክስ ሳይመሠረትባቸው ለረዥም ወራት ታሥረው በፖሊስ ምርመራ እየተደረገባቸው የሚቆዩበት ሂደት ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ዋነኛ መንሥዔ ነው፡፡ በፖሊቲካ ምክንያቶች የታሠሩ ዜጎች ፍርድ በሚቀርቡ ጊዜ ሁሉ ከሚያሰሟቸው አቤቱታዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የዕምነት ቃል እንዲሰጡ በመርማሪ ፖሊሶች ሰብዓዊ ክብራቸውን የሚነኩ የማሠቃያ ድርጊቶች ይፈጸሙባቸዋል፣ ከፍርድ በፊት ነጻ ሆነው የመታየት መብታቸው ተጥሶ እንደወንጀለኛ ይቆጠራሉ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ይከለከላሉ፡፡

ይህን መሰሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የሕግ ሥርዓቱን ለፖሊቲካ ሥርዓቱ ተንበርካኪ የማድረግ እርምጃ ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የመጠበቅ እንዲሁም ለመብቶች መከበር አስፈላጊውን ኹኔታ የማሟላት ግዴታ ያለበት መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ በማድረግ በሕግ ከለላ ሥር ያሉ ሰዎችን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር፣ የማስከበርና ለመብቶቹ መከበር አስፈላጊውን ኹኔታ የማሟላት ግዴታውን እንዲወጣ ሰመጉ ያሳስባል፡፡

## የሰመጉ አድራሻ

ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ

ኢ.አ ስታዲየም አጠገብ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢሜይል: info@hrco.org.et

ድረ ገጽ: www.hrco.org.et

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: monitoringcomplaints@hrco.org.et

### ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ሐዋሳ (ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ(+251)046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

ባሕርዳር (ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ(+251)058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ነቀምቴ (ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 057 661-5014፣ ፖ.ሳ.ቁ 463

ድሬደዋ (ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251)025 811 9150 ፖ.ሳ.ቁ 2596

ጅማ (ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 147 211 5434

አዲስ አበባ (ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና)፡

ስ.ቁ (+251) 011 551-7704፣ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

### የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት

አቶ ብዙአየሁ ወንድሙ - ሰብሳቢ

አቶ ዘየደ ገ/ጻዲቅ - አባል

አቶ ዳን ይርጋ - አባል

አቶ ደረጀ መላኩ - አባል

አቶ ሱራፍኤል ግርማ - አባል

# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)፤ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም መሆኑ ይታወቃል። ሰመጉ ከተቋቋመበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 24 ዓመታት ሁለንተናዊ ሐገራዊ ተልዕኮ በመያዝ በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ በነደፋቸው በርካታ ፕሮግራሞች አማካኝነት የሰብዓዊ መብት መከበር፣ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በመታገል በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ እያበረከተም ይገኛል።

ይህን ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ፣ የጥሰቱ ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁ፣ የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ በሕዝብና በመንግሥት አስፈጻሚ አባላት ዘንድ እንዲዳብር፣ የተፈጸሙ ጥፋቶች እርማት እንዲያገኙ በአጠቃላይም የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ብዙ ሠርቷል አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛል።

ዋና ዋናዎቹ የሰመጉ የሥራ ኃላፊነቶችም፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መከታተልና ለሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በማሳወቅ እንዲታረም ማድረግ፣ የሕግ ድጋፍ መስጠት፣ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ በሰብዓዊ መብቶች ላይ ትምህርት መስጠት፣ የወጡና የሚወጡ ሕጎች በትክክል ስለመተግበራቸው መከታተል፣ የሰብዓዊ መብት አያያዝን መከታተል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቁን ማረጋገጥ፣ መመርመርና መግለጫ ማውጣት ናቸው።

በእስካሁኑ ቆይታው ሰመጉ 36 መደበኛ መግለጫዎችና 139 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ከእነዚህም ባሻገር ሕዝቡ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ትግበራ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል ተከታታይ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት የአድቮኬሲ እና የሕግ ድጋፍ ሥራዎችን አከናውኗል፡ ፡ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ዐቅም በፈቀደለት መጠን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

**ማሳሰቢያ**

**1. መልዕክተ ሰመጉ በአውሮፓ ኅብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚታተም የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ /ሰመጉ/ ልሣን ነው። በልሣኑ ላይ የሚታተሙ ጽሑፎች በጠቅላላ የአውሮፓ ኅብረትን ዐቋም የማያንጸባርቁ መሆናቸውን ሰመጉ ለአንባቢያን ያስታውቃል።**

**2. የሰመጉ ድርጅታዊ ዐቋም የሚገለጸው በርእሰ አንቀጽ ላይ ብቻ መሆኑን እናስታውቃለን።**

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!

HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights





# ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እና የሥልጣን ገደብ በኢትዮጵያ

**ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትና የመንግሥት የሥልጣን ገደብ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል የሕግ መምህር የሆነው <u>ውብሸት ካሣው</u> በሁለት ክፍል ትንታኔ ያቀርብልናል። በዚህ ወር ዕትም በሚስተናገደው የመጀመሪያ ክፍል ንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔው የቀረበ ሲሆን፣ በቀጣዩ ዕትም የዚህ መብት አከባበር የመንግሥት ሥልጣንን በመገደብ ረገድ የሚኖረው ሚና ከተግባራዊነቱ ዐውድ አኳያ ይተነተናል።**

ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ኢትዮጵያ ተቀብላ የሕጎቿ አካል ባደረገችው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ዓለም ዓቀፍ መግለጫም ሆነ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ሕገ መንግሥት የሚከተለው ትርጉም ተሰጥቶት እናገኘዋለን:- ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ማንም ሰው በሐገር ውስጥም ሆነ ከሐገር ውጭ ምንም ዓይነት ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በኅትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው ማንኛውም ዓይነት የማሠራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃ እና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበል እና የማሠራጨት ነጻነትን የሚያካትት መብት ነው። ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት የመያዝ መብት ዋናው የግል መብት ሲሆን ይህ መብት ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መነሻ እና መሠረትም ጭምር ነው። ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በውስጡ የፕሬስ ነጻነት እና የመናገር መብትን (freedom of speech) የሚያካትት ሲሆን ለሌሎች የሰብዓዊ መብቶች መከበር እና በተግባር ላይ መዋል መሠረታዊ መብት ሆኖ እናገኘዋለን። አንድ ሰው የመናገር ወይም ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቱን ተጠቅሞ የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ውሳኔዎችን ካልተቸ እና በነጻነት ካልተናገረ በሐገሪቱ የዕለት ተዕለት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ በተግባር ላይ እንዲውሉ ንቁ ተሳትፎ ከማድረግ አንጻር እንዲሁም መንግሥት የመብት ጥሰት ሲፈጽም ለመቃወም አስቸጋሪ ይሆንበታል።

በሌላ በኩል ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ምንጭ መሠረት የሆነው የሕዝቦች ሉዓላዊነት መገለጫ ሲሆን ሕዝቦች ስለ መንግሥት የጋራ አቋም፣ ሐሳብ እና አመለካከት በመያዝ በምርጫ ፈቃዳቸውን በመግለጽ የሥልጣን ባለቤትነታቸውን የሚያረጋግጡበት አንዱ መንገድ ነው። በዚሁ መንገድ ሕዝቦች የመንግሥት ፖሊሲዎችን እና ውሳኔዎች ላይ ሃሳባቸውን በመግለጽ ማለትም በመቃወምም ሆነ በመደገፍ እንዲያም ሲል በሕዝባዊ ውይይቶች የጋራ ዐቋም በመያዝ መንግሥትን ከሥልጣን ለማውረድ የሚጠቅም የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበት እና ለመንግሥት ሥልጣን ገደብ የሚበጅበት ዋናው መንገድ ነው። በተጨማሪም የመንግሥትን የቀን ተቀን ውሳኔዎች ለሕዝብ ውይይት ክፍት በማድረግ እና በማጋለጥ ሕዝቡ ሐሳቡን እንዲገልጽ በማድረግ መንግሥት ለውሳኔዎቹ ኃላፊ እንዲሆን፣ ተጠያቂነት እንዲሰፍን እንዲሁም ሥልጣን ገደብ እንዲኖረው በማድረግ በኩል የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለዴሞክራሲያዊ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሐሳብን በነጻነት. . .

ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሐሳቦች እና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸር አስፈላጊ እና መሠረታዊ የሆነ መብት በመሆኑ የሕግ ጥበቃ እንደሚደረግለት እና ማንም ሰው የመሰለውን ዐቋም መያዝ እንደሚችል እንዲሁም ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነጻነት እና የተለያዩ ሐሳቦችንና አስተያየቶችን ማስተናገድ እንዳለበት ይደነግጋል:: ሕገ መንግሥቱ እንደማንኛውም መብቶች እዚህ መብትም ላይ ገደብ እንደሚደረግ ገልጾ መብቱ ላይ ገደብ ለማስቀመጥ ሦስት ነገሮች መሟላት እንዳለባቸው ያመለክታል:: እነዚህም ገደቦች በሕግ መደንገግ እንዳለባቸው፣ ማንኛውም ሐሳብ እና መረጃ በአስተሳሰባዊ ይዘቱ እና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ/ሊገደብ እንደማይገባው እና ገደቦቹ ከሚከተሉት አራት ዓላማዎች አንዱን ለማሳካት ብቻ ሲሆን በመብቱ ላይ ሕጋዊ ገደብ ማድረግን ይፈቅዳል:: እነዚህም ዓላማዎች የወጣቶችን ደኅንነት ለመጠበቅ፣ የሰውን ክብር እና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከልከል በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል:: በተመሳሳይ መልኩ የመገናኛ ብዙኃንና መረጃ ነጻነት ዓዋጅ ቁጥር 590/2000 የመገናኛ ብዙኃን ነጻነት ቅድመ ምርመራን በማንኛውም መልኩ በመከልከል መንግሥታዊ አካላትም የመገናኛ ብዙኃንን ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ የመቀበል እና የማሠራጨት፣ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትንተና የማቅረብ ወይም የተለያዩ ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሂደት የመሳተፍ መብታቸውን እንዲያከብሩ ኃላፊነት ጥሎባቸዋል:: በመሆኑም ይህ ዓዋጅ የመገናኛ ብዙኃን የመንግሥት አሠራሮችን በመተቸት እና አስተያየት በመስጠት የመንግሥትን አግባብ ያልሆኑ ውሳኔዎች እና ሕገወጥ አሠራሮችን በመንቀፍ የሥልጣን ገደቡን እንዲያከብር በማድረግ በኩል የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ መደላድል ለመፍጠር ይሞክራል::

*<u>ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ የተጣሉ የሕግ ገደቦች (LEGAL RESTRICTIONS)</u>*

በኢትዮጵያ በዚህ መብት ላይ የተለያዩ ገደቦች የሚያስቀምጡ የተለያዩ ሕጎች ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ ገደቦች የመብቱን በተግባር ላይ መዋል ፈተና ላይ እስከሚጥሉ ድረስ መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን፣ ከሌሎች ሐገሮች ልምድም ሆነ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚጣጣሙ አይመስሉም:: በመጀመሪያ ደረጃ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግን እንመልከት:: በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 244 ላይ መንግሥትን ማዋረድ፣ ስም ማጥፋት፣ እና መስደብ ወንጀል ሆኖ እናገኘዋለን የሌሎችን ሐገራት ልምድ (ለምሳሌ በአሜሪካ ማንኛውም ንግግር ላይ ገደብ ሊደረግ የሚችለው ንግግሩ ቅርብ እና ሊደርስ የሚችል አደጋ (imminent lawless action) የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ነው) ስንመለከት ግን እንደዚህ ዓይነት ገደቦች (በተለይም የመንግሥትን ስም ማጥፋት የሚል ወንጀል) የተለመዱ አይደሉም:: በተለይም መንግሥት ማንኛውንም ትችት እንደትችት መቀበል እና ውሸት ሁኖ ሲያገኛቸው ማስተባበል እውነት ሲሆኑ ደግሞ ማረም ሲገባው የማጣራቱን ጉዳይ ግለሰቦች ጫንቃ ላይ መጣሉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ በዚሁ ምክንያት ግለሰቦችን ለወንጀል ተጠያቂነት መዳረግ ሐሳባቸውን በነጻነት እንዳይገልጹ መሰናክል መሆን ነው::

በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 486 መንግሥትን፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ወይም በሥራቸው ላይ ማናቸውንም የሐሰት ጥርጣሬዎችን በመንዛት የሕዝብን አስተሳሰብ ያናወጠ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ማሳጣት ወይም ሌላ ዘዴ በመጠቀም ጥርጣሬን ማስፋፋት ወይም ጥላቻን ማነሣሣት ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል:: ይህን አንቀጽ ስንመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ማንም ሰው በእርሱ ያስተሳሰብ ደረጃ እና የማጣራት ዐቅም ሆኗል ወይም እውነት ነው ብሎ ያሰበውን ጉዳይ ነው ሊናገር ወይም ሊጽፍ የሚችለው:: ነገር ግን ገና ለገና የተነገረውን ወሬ ለመዘገብ ወይም ለማውራት የጉዳዩን እውነተኛ መሆን አጠራጣሪ የመሆን ጉዳይ

ወደ ገጽ 5 የዞረ



# ሐሳብን በነጻነት. . .

በምን ዓይነት መሥፈርት ተመርምሮ ነው ‹‹ሐሰት አወራ›› የምንለው? ወይስ ግለሰብን እንደ መንግሥታዊ አካል ለእያንዳንዱ ለሚያወራው ነገር መርማሪ ቡድን እንዲያቋቁም እየፈረድንበት ነው? በተጨማሪም ሕጉ “ማንኛውንም ማሳጣት” ሲል ምን ማለቱ ነው? ማንም ሰው ከበቂ ጥርጣሬ (ልብ በሉ እርግጠኝነት አላልኩም) ተነሥቶ መንግሥትን በማጋለጥ እና በመተቸት መንግሥት ስለ እውነተነቱ ለሕዝብ ግልጽ መግለጫ እንዲሰጥ እውነት ከሆነም ማስተካከያ እንዲያደርግ ሐሳብ ካልተሰጠ በየትኛው መንገድ ነው ታዲያ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ተረጋግጧል ለመንግሥትም ተገቢው ገደብ ተደርጎበታል ማለት የምንችለው? ስለዚህ ይህ አንቀጽ ቢያንስ የተለያዩ መለኪያዎች፣ ማብራሪያዎች ሊታከሉበት የሚገባ ከመሆኑም በላይ አዳንዶቹ ወንጀል ናቸው ተብለው የተጠቀሱት ነገሮች እንዲያውም ወንጀል ሊሆኑ የማይገባቸው በመሆናቸው ሙሉ ለሙሉ ሊወጡ ይገባል:: ለምሳሌ በመንግሥት ላይ ጥርጣሬን እና ጥላቻን ማስፋፋት የሚለው መውጣት አለበት ምክንያቱም ሕዝቦች በመንግሥት ላይ ያላቸውን ቅሬታ እንዳያቀርቡ መሰናክል ሊሆን የሚችል በመሆኑ::

ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በተለይም የፕሬስ ነጻነትን በተመለከተ ከተጣሉ የሕግ ገደቦች ሌላኛው ሕግ ደግሞ በጸረ ሽብርተኝነት ዐዋጅ ቁ652/2001 በአንቀጽ 6 ላይ የተካተተው ሽብርተኝነትን ማበረታታትን በተመለከተ የሚደነግገው አንቀጽ ነው:: ዐዋጁ ማንኛውም ሰው መልዕክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የኅብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይም በሙሉ በዚሁ ዐዋጅ የሽብርተኝነት ድርጊት ናቸው ተብለው የተጠቀሱትን “እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈጸም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሣሡ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በሌላ በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ እንደሆነ ከ 10 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል” ይላል:: እዚህ ጋ አትኩሮት መስጠት ያለብን ነገር ሕጉ ከግምት ውስጥ ያስገባው የድርጊት ፈጻሚውን ሐሳብ፣ የሐሳቡን አደገኛነት ወይም ቅርብ እና ሊደርስ የሚችል (the imminence or presence of the danger) አደጋ ስለመኖሩ ሳይሆን ከሦስተኛ ወገኖች የመረዳት ሁኔታ አንጻር ብቻ የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህም ሰዎች ከራሳቸው ሐሳብ እና ድርጊት ይልቅ በቀላሉ እና በእርግጠኝነት ሊረዱት ስለማይችሉት የሦስተኛ ወገኖች የሐሳብ መረዳት እንዲጨነቁ በማድረግ በፍርሐት ሐሳባቸውን ከመግለጽ እንዲቆጠቡ ከማድረጉም በላይ እራሳቸው ላይ ቅድመ ምርመራ (self censorship) እንዲፈጽሙ በማድረግ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል የሚያደርግ እና የፕሬስ ነጻነትን የሚገድብ እና የሚያቀጭጭ ሆኖ እናገኘዋለን:: በተጨማሪም ሕጉ ‹‹በተዘዋዋሪ መንገድ ማበረታታት ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የሚገፋፋቸው›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እና ምን ዓይነት ድርጊቶች በግልጽ ወንጀል እንደሆኑ በግልጽ የማያመለክት በመሆኑ ከወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ሊጋጭ በሚችል መልኩ ፍርድ ቤቶች በሕግ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት በማመሳሰል (crime by analogy)እንደ ወንጀል እንዲቆጥሩ ሊያደርግ ይችላል:: ስለዚህ ይህ ሕግ ሊሻሻል እና ግልጽነትን በሚፈጥር መልኩ በአዲስ መልክ ሊቀረፅ የሚገባው ሆኖ እናገኘዋለን::

*በዐርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር የሆነው ውብሸት ካሣው በአሁኑ ሰዓት በአ.አ.ዩ ለማስተርስ ዲግሪው ማሟያ በሕገ መንግሥትና በ‹‹ፐብሊክ›› ሕግ ላይ ጥናቱን በመሥራት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በሰመጉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::*

# የኮምፒውተር ዓዋጅ _ ነጻ ሐሳብን የመገደብ ቀጣዩ እርምጃ?

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት 30 ቀን 2008ዓ.ም ‹‹የኮምፒውተር ዓዋጅ›› አጽድቋል:: የሕግ ባለሙያው ቢንያም አባተ የዓዋጁን አንደምታ ከሕግና ከፖሊቲካ ዕይታ አኳያ ይተነትናል::

የሕዝቦች የዕውቀት እድገትና ሐሳብን በነጻነት መግለጽ ከሐገር ሉዓላዊነት በላይ እጅጉን ሥጋት ላይ የሚጥለው የኢትዮጵያ መንግሥት ከሰሞኑ የኢንተርኔት አገልግሎትን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችለውን “የኮምፒውተር ዐዋጅ” አጽድቋል:: መንግሥት ይህንን ሕግ ለማርቀቅ የተነሣሣው “በሐገሪቱ እየጨመረ ነው” ያለውን ኮምፒውተርን እና/ወይም ኢንተርኔትን መሠረት ያደረጉ ወንጀሎችን (የሳይበር ጥቃቶች) ለመከላከል እንዲሁም በመስፋፋት ላይ ያሉትን ቁልፍ የመሠረተ ልማት አውታሮች ተጋላጭነትን ታሳቢ በማድረግ መሆኑን ሲገልጽ ሰንብቷል:: ይሁን እንጂ እንደ ብዙዎቹ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፤ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች አክቲቪስቶች የዚህ ሕግ ቀዳሚ ዓላማ በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ነጻ መድረክነት እየጎለበተ የመጣው ፖለቲካዊ ውይይትና የዜጎች ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለመንግሥት ሥጋት እየሆነ በመምጣቱ መሆኑን ይገልጻሉ::

መረጃ እና ኮምፒውተርን መሠረት ያደረጉ ቁልፍ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ደኅንነት በማረጋገጥ ለሐገሪቱ የሰላም፤ የልማት እና የዴሞክራሲ መርኃ ግብሮች ማስፈጸሚያ እንዲሆኑ ማስቻልን ዓላማው አድርጎ በ2006 ዓ.ም. እንደገና የተቋቋመው ‹‹የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ›› (INSA) በተደጋጋሚ የሳይበር ጥቃቶች እየበረከቱ መምጣታቸውን ሲገልጽ ቆይቷል:: ከእነዚህ የሳይበር ጥቃት ዒላማ ሆነዋል ከሚባሉት የፋይናንስ እና ትልልቅ የመንግሥት ተቋማት በተጨማሪ ግለሰቦችም በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ ስብዕናቸውን የሚያጎድፉ ጥቃቶች እንደሚፈጸምባቸው ሲገልጽ ይደመጣል:: የ INSA ጄኔራል ዳይሬክተር ተክለ ብርሃን ወልደ አረጋይ በ ‹ኢቲቪ› በተላለፈ ዝግጅት ላይ በሰጡት ገለጻ በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ “ጾታዊ የበቀል ጥቃት” (revenge pornographic acts) የደረሰባቸው በርካታ ዜጎች መፍትሔ ፍለጋ የተቋሙን በር አንኳኩተዋል:: ለዚህም ይመስላል ተቋሙ በተደጋጋሚ የረቂቅ ሕጉን አስፈላጊነት ሲያሳስብ የቆየው:: ሆኖም ይህ ሕግ አለቅጥ የተለጠጡ አንቀጾችን የያዘ መሆኑ ብዙዎችን ከወዲሁ ሥጋት ላይ መጣል ብቻ ሳይሆን ዓዋጁንም በጥርጣሬ እንዲያዩት አስገድዷል::

በዐዋጁ አንቀጽ 13 “በሰዎች ነጻነትና ክብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች” በሚል ርእስ ሥር የሠፈረው ድንጋጌ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲን ተደጋግሞ የተገለጸ “ሥጋት” መነሻ ያደረገ ይመስላል:: በዚህ አንቀጽ መሠረት የኮምፒውተር ሥርዓትን በመጠቀም በጽሑፍ፤ በንግግር፤ በምስል አልያም በቪዲዮ አማካይነት የሚተላለፉ መልዕክቶችን በመጠቀም በግለሰብ ላይ ወይም በቤተሰቦቹ ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ያስፈራራ ወይም የዛተ፤ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል:: በዚህ አንቀጽ የዜጎችን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት (The Right to Privacy) ለማስከበር የቆመ የሚመስለው ረቂቅ ሕግ የግለሰቦችን በነጻነት ሐሳብን የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚሸረሽር አንቀጽ አካትቷል::

በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የማኅበራዊ ድረ-ገጾችን በመጠቀም የሚተላለፍ መልዕክት በኅብረተሰቡ መካከል የፍርሐት ስሜት፣ አመፅ፣ ኹከት ወይም ግጭት እንዲፈጠር አነሣሥቷል ወይም ያነሣሣል ተብሎ ከታመነ እስከ ሦስት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እሥር ያስከትላል:: የብዙዎችን ትኩረት የሳበው ይህ አንቀጽ በመደበኛ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች መንሸራሸሪያ ላጣው የዜጎች ነጻ ድምፅ አንጻራዊ መድረክ እየሆኑ የመጡትን የማኅበራዊ ድረ ገጾች ሚና የሚገድብ መሆኑ አያጠያይቅም:: ይህም የሕዝቡን በመረጃ ቴክኖሎጂ የመጠቀም ተስፋ የሚያጨልም ብቻ ሳይሆን የማኅበራዊ ድረ ገጾችን የማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነጻ የውይይት መድረክነት የሚያጠብ ይሆናል:: ከሁሉም በላይ በቋፍ ላይ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል



# የኮምፒውተር ዓዋጅ

ያለውን የኢንተርኔት አገልግሎትና አንጻራዊ የገለልተኛ መረጃ አቅርቦት ይበልጡኑ የሚያከስመው ይሆናል::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ማኅበራዊ ድረ ገጾች በዓለማችን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያላቸው የጎላ ተጽእኖ በግልጽ የሚታይ ነው:: በተለይም በጸደይ አብዮት (Arab Spring) አምባገነን መንግሥታትን ከሥልጣን እስከ ማስወገድ የደረሰውን ሕዝባዊ ንቅናቄ የማቀጣጠል ብቃታቸው በኢትዮጵያም እንዳይከሰት ፍርሐት ያደረበት መንግሥት የማኅበራዊ ድረ ገጾችን አስተዋጽዖ ለማኮላሸት አገልግሎታቸውን ከማቆራረጥ እስከ መገደብ የሚደርስ እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል::

ከነዚህ እርምጃዎች አንዱ ከተገቢው በላይ የሆነ ክፍያ በመጠየቅ በኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ላይ ኢኮኖሚያዊ ጫና መፍጠር ነው:: ከአገልግሎት ክፍያውም በላይ የኢንተርኔት አቅርቦት ጥራቱ እጅጉን አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል:: በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሐገራችን የተለያዩ ክፍሎች የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ በክልሎች በተለይም በኦሮሚያ የሚታየው የኢንተርኔት አቅርቦት መቆራረጥ መንግሥት ተቃውሞውን ለማፈን የሄደበትን ርቀት የሚያሳዩ ናቸው:: ይህ የኢትዮጵያ መንግሥት እርምጃ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 የተቀመጠውን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የሚሸረሽር ነው::

በቅርብ ጊዜ የወጡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ የኢንተርኔት አገልግሎት ማቅረብ የቻለችው ከአጠቃላይ የሕዝብ ብዛቷ ለ3.7% ዜጎቿ ብቻ ሲሆን፣ ይህም በእርስ በርስ ጦርነት በመታመስ ላይ ካለችው ደቡብ ሱዳን እጅጉን ያነሰ መሆኑ አሳሳቢ ያደርገዋል (ደቡብ ሱዳን ለ15.9% ዜጎቿ ኢንተርኔትን ማዳረስ ችላለች):: ይህ ቁጥር ኢትዮጵያን ከመጨረሻዎቹ 10 የዓለማችን ሐገራት አንዷ ያደርጋታል:: ሁኔታውን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ በሐገራችን ብቸኛው የኢንተርኔት አቅራቢ የሆነው ኢትዮ ቴሌኮም በሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ ውድነት ከዓለም ቀዳሚ መሆኑ ነው::

ሌላው የኢትዮጵያ መንግሥት የዜጎቹን ድምፅ ለማፈን የሚጠቀምበት መንገድ ሐገሪቷን ኮምፒውተርን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል በዐዋጅ ቁጥር 808/2013 እንደገና የተቋቋመውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲን (INSA) ዜጎችን ለመሰለል መጠቀሙ ነው:: ይህ መንግሥታዊ ተቋም የስልክ ንግግሮችንም ሆነ ኢንተርኔትን መሠረት ያደረጉ የመገናኛ ዘዴዎችን የመሰለል ሙሉ ሥልጣን በዐዋጁ የተሰጠው ሲሆን በርካታ ድረ ገጾችንም በመዝጋት የዜጎችን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ እና መረጃ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት በመገደብ ይታወቃል::

እጅጉን ዝቅተኛ የአገልግሎት ሽፋን፤ ከአቅርቦት ጥራቱ ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ ክፍያ እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ያልተገደበ የስለላ እና የስልክና ኢንተርኔት ግንኙነት የመጥለፍ ሥልጣን የኢትዮጵያዊያንን የንግግር ነጻነትና የመረጃ ፍሰት ለመገደብ በቂ መስሎ ያልታየው የኢትዮጵያ መንግሥት ተጨማሪ አፋኝ ሕግ አርቅቆ በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ለተዋቀረው ምክር ቤት በማቅረብ አስጸድቋል:: ይህ ሕግ ዜጎችን ከፍርሐት አረንቋ የሚከት መሆኑ የሚጠበቅ ነው:: አንድ ሕግ ሲረቀቅ ሐገሪቱ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን መጪው ጊዜንም ከግምት ያስገባ መሆኑ ዕሙን ነው:: ከዚህ አንጻር ኮምፒውተርንና የኢንተርኔት መረብን በመጠቀም የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሌሎች ሐገራት እያደገ መምጣትና ሐገሪቱ ከኢንተርኔት ቴክኖሎጂ ጋር እያሳደገች የመጣችውን ቁርኝት ከተመለከትን የሕግ ማዕቀፍ የማዘጋጀቱ አስፈላጊነት አይካድም:: ሆኖም ይህ ዐዋጅ ልክ እንደ ጸረ ሽብር ሕጉ ሁሉ የዜጎችን በነጻነት ሐሳብን የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚሸረሽር ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን አንደበት በፍርሃት ለመሸበብ የተቀረፀ መሆኑ ይታመናል::

በአጠቃላይ የኢንተርኔት አገልግሎት በኢትዮጵያ በበቂ አቅርቦት የማይገኝ ብቻ ሳይሆን የጥራት ችግርም ያጕሳቆለው መሆኑ በግልጽ የሚታይ እውነታ ነው:: ከሁሉም በላይ አሳሳቢ የሆነው ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በተከታታይ እያወጣቸው የሚገኙት አፋኝ ሕጐች ቀዳሚ ዓላማቸው የነጻ መረጃ ፍሰትን እና የንግግር ነጻነትን መገደብ፤ እንዲሁም የዜጐችን አንደበት በፍርሃት መሸበብ መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ መንግሥት የዜጐችን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብት ለመገደብ የሚያደርገው ያልተቋረጠ ጥረት በራሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከመሆኑም በላይ በሌሎች ሰብዓዊ መብቶች መከበር ላይ የሚያደርሰውን አፍራሽ ተጽእኖ ልንገነዘበው ይገባል:: ይህንንም ተገንዝበን ዛሬም ሰላማዊ ትግላችንን ሳናቋርጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ራሱ ያወጣውን ሕገ መንግሥት እንዲያከብር እንጠይቃለን::

## ከምርመራ ማኅደር

# የ140ኛና 141ኛ ልዩ መግለጫዎች ዳሰሳ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ 140ኛ ልዩ መግለጫውን በቅርቡ ይፋ አድርጓል። ‹‹በመንግሥት የጸጥታና ታጣቂ ኃይሎች በዜጎች ላይ የሚፈጸም አሠቃቂ ግድያ፣ ሕገ ወጥ እሥር፣ ድብደባ፣ ማስፈራራትና ማዋከብ በአስቸኳይ ይቁም!›› በሚል ርእስ የወጣው ልዩ መግለጫ በኦሮሚያ ክልል የደረሰውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በዝርዝር የሚያሳይ ነው፡ ፡ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን ባለመቀበል በመላው ኦሮሚያ ከተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የተከሰተው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ይፋ የሆነበት ይህ የምርመራ ውጤት በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ 18 ዞኖችና 342 ወረዳዎች ውስጥ ዘጠኝ ዞኖችንና 33 ወረዳዎችን የሸፈነ ነው።

በልዩ መግለጫው ላይ በተጠቀሰው መሠረት የመጀመሪያው የተቃውሞ መነሻ ምዕራብ ሸዋ ዞን ደንዲ ወረዳ ጊንጪ ከተማ ነው። መነሻው በጊንጪ ከተማ የሚገኘውን የጊንጪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ኳስ ሜዳ የጊንጪ ከተማ ከንቲባ፣ የወረዳው አስተዳዳሪና ሌሎችም ባለሥልጣናት ሸንሽነው ለግለሰቦች በመስጠታቸውና የተማሪዎቹን መጫወቻ ሜዳ የተረከቡት ግለ ሰቦች ሥፍራውን በማጠራቸው የጊንጪ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ድርጊቱን በመቃወም ኅዳር 02 ቀን 2008ዓ.ም ተቃውሞ ማሰማታቸው ነው።

የተማሪዎቹን ተቃውሞ ተከትሎ የጊንጪ ከተማ ከንቲባና ሌሎችም ባለሥልጣናት ግንባታው እንደሚቀጥል ገልጸው ግንባታው እንዲቆም ተደረገ። ከዚህ በመቀጠል ለክፍለ ዘመናት ተጠብቆ የቆየው የጭልሞ ደን ለግለሰብ መሸጡን ተማሪዎች በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ፤ ሕዝቡም ሰልፉን ተቀላቅሎ ተቃውሞውን አሰማ። ከደኑ ይዞታ ሦስት የእግር ኳስ ሜዳ ያህል ስፋት ባለው መሬት ላይ የነበረ የሐበሻ ጥድ፣ የኮሶ እንዲሁም ሌሎች ሐገር በቀል ዕጽዋት ዛፎች በመጨፍጨፋቸው ተቃውሞው እየበረታ ሲሄድ የደኑ መጨፍጨፍ ቆሞ በነበረበት እንዲቆይ ተደረገ። ከዚህ በኋላ ‹‹የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ማስፋፋትን እንቃወማለን›› በማለት ተቃውሞው ቀጠለ። የሕዝባዊ ተቃውሞውን እንቅስቃሴ ለማስቆም መንግሥት በወሰደው የኃይል እርምጃ የበርካታ ዜጎች ሕይወት ያለፈ ሲሆን፣ የሰመጉ ባለሙያዎች በተጨባጭ ማስረጃ አጠናቅረው በተዘጋጀው ልዩ መግለጫ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች የተገደሉ 103፣ የቆሰሉ 57፣ ማሠቃየት የተፈጸመባቸው 22፣ የታሠሩ 84፣ የደረሱበት የማይታወቅ 12 ዜጎችን ማንነት ይፋ አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አመያ ወረዳ በኩዮ ቁሊት (ቀርሳ ቁሊት)፣ ወረ ወገሪ (በሬዳ) እንዲሁም አብሌ መድኃኔዓለም ቀበሌዎች ከታኅሣሥ 02 ቀን 2008ዓ.ም ሌሊት ጀምሮ ማስተር ፕላኑን ለመቃወም ከወጡ ሰልፈኞች መካከል ጥቂቶቹ በአካባቢው ከ30 ዓመታት በላይ የኖሩ የአማራ ብሔር ተወላጆችን መኖሪያ ቤቶች ከነሙሉ ንብረቶቻቸው እንዳቃጠሉባቸው በልዩ መግለጫው ተመልክቷል። በዚሁ ሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት በተጎጂዎቹ አርሶ አደሮች መኖሪያ ቤት ውስጥ የነበረ ለሽያጭ የተዘጋጀ በርበሬና የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ምርት ወድሟል፣ ማሳ ላይ የነበረ እህልም ተቃጥሏል። በዚሁ ጥቃት ምክንያት በርካታ ሰዎች ተፈናቅለው ወደ ኹዳድ2፣ ዳርጌ፣ ዋልጋ እንዲሁም ወልቂጤ መሰደዳቸው ተገልጿል። በልዩ መግለጫው መሠረት፣ የተጠቀሰውን የንብረት ውድመት ተከትሎ በኩዮ ቁሊት ቀበሌ የአማራ ተወላጆች በወሰዱት የአጸፋ እርምጃ ቁጥራቸው 96 የሚሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ቤት ተቃጥሏል። ይህን መሰሉን ሕዝብን በሕዝብ ላይ የማነሣሣት ድርጊት የፈጸሙት በዋነኛነት የራሳቸው ያልሆነውን መሬትና ሀብት

ወደ ገጽ 9 ዞሯል



# የ140ኛና 141ኛ

ለመንጠቅና ለመክበር የሚፈልጉ ጥቂት የአካባቢ ሀብታሞችና ጥቅም ፈላጊ ባለሥልጣናት መሆናቸውን መግለጫው ያመለክታል።

በመግለጫው ማብቂያ ላይ፣ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በዜጎች ላይ የፈጸሙት ግድያ፣ በጥይት ማቁሰል፣ በድብደባ ማሠቃየት፣ እሥራት በማንኛውም መለኪያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ሰመጉ አሳስቧል። በሕዝቡ በተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ሰበብ የሕይወት፣ የአካል፣ የንብረት ጉዳት ያደረሱትና ጉዳቱ እንዲደርስ ያዘዙት ኃላፊዎች በአስቸኳይ በሕግ እንዲጠየቁ፣ ለሟቾች ቤተ ሰቦችና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣ የታሠሩ እንዲፈቱ ጥሪውንም አቅርቧል።

ሰመጉ ግንቦት 24 ቀን 2008ዓ.ም ባወጣው 141ኛ ልዩ መግለጫ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የማንነት ጥያቄ በሚያነሡ ዜጎች ላይ የሚፈጸም ግድያ፣ ሕገ ወጥ እሥራት፣ አፍኖ መሠወር፣ ማፈናቀልና ንብረት መንጠቅ በአስቸኳይ እንዲቆም ጠይቋል። በዚህ ልዩ መግለጫው፤ ከወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የቅማንት ሕዝብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ የቁጫ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ የኮንቶማ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄን ተከትሎ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተዘርዝረዋል።

ከወልቃይት ሕዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ፡-

- 34 የወልቃይት ተወላጆች ላይ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል፣
- የማንነት ያቄ በማንሣታቸው ምክንያት 93 ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ታፍነው ተወስደው እስካሁን ድረስ ያሉበት አይታወቅም፣
- ከማንነት ጥያቄው ጋር በተያያዘ 17 ሰዎች ሕገ ወጥ እሥራት ተፈጽሞባቸዋል፣
- ከቋንቋ፣ ከባሕል፣ ከኢኮኖሚ፣ ከፍትሕ አሰጣጥና ከአስተዳደር ጋር በተያያዘ በወልቃይት ተወላጆች ላይ አድልዎና በደል ተፈጽሞባቸዋል።

የቅማንት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ኮሚቴና ምስክሮች ለሰመጉ ባቀረበው አቤቱታ መሠረት፡-

- ከማንነት ጥያቄው ጋር በተያያዘ 22 ሰዎች ተገድለዋል፣
- 10 ሰዎች ቆስለዋል፣
- ከ148 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ወድሟል

የቁጫ ሕዝብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪ ተወካዮች ለሰመጉ ባቀረቡት አቤቱታ እንደገለጹት፡-

- 42 ሰዎች የማንነት ጥያቄ አንሥታችኋል ተብለው ታሥረው የዋስትና መብትም ተነፍገው ይህ መግለጫ ይፋ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ፍርድ ሳያገኙ ዐርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት በእሥር ላይ ይገኛሉ፣
- ከዚሁ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ነፍስ ያጠፉ ሰዎች ለሕግ አልቀረቡም፣
- ከ100 በላይ ዜጎችን በጥይት ያቆሰሉ ለሕግ አልቀረቡም፣
- ብዛት ያላቸው የማኅበረሰቡ አባላት ከመንግሥት ሥራ ተባርረዋል፣ ከእርሻቸው ተፈናቅለዋል፣ ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይገኙ ተደርገዋል፣ ነጋዴዎች እንዳይነግዱ ተከልክለዋል።

የኮንቶማ ማኅበረሰብ የማንነት ጥያቄ አስተባባሪዎች በገለጹት መሠረት፡-

- የማንነት ጥያቄ በማንሣታቸው ምክንያት የማኅበረሰቡ አባላት ለሕገ ወጥ ግድያ፣ ለእሥራትና ለንብረት ውድመት ተዳርገዋል።

በመግለጫው ማጠቃለያ ሰመጉ፤ መንግሥት ለሕዝብ ጥያቄዎች የኃይል ምላሽ በመስጠት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ከመጣስ ይልቅ ሕገ መንግሥቱን፣ የአፍሪካን የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተርና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችን በማክበር የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከበርና ለመብቶች መከበር አስፈላጊውን ሁኔታ እንዲያሟላ ጠይቋል።

# የልማታዊ መንግሥት ዕሳቤ ትግበራ ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር

በሱራፍኤል ግርማ

የልማታዊ መንግሥት ርዕዮተ ዓለምን ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን የሚገልጸው ገዢው ፓርቲ በተደጋጋሚ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እየፈጸመም ቢሆን ከምዕራባዊያን ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እየጎረፈለት ይገኛል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው በኢትዮጵያ ያለው አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ የአጠቃላይ ሐገራዊ ምርት ዕድገትና አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት ናቸው፡፡ ግዙፍ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፣ ለውጭ ባለሀብቶች ሰፊ የእርሻ መሬቶችን ማከራየትና በውጭ ባለሀብቶች ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ ላይ የተመሠረተ የኢንደስትሪ ማስፋፋት ዋና ዋና የመንግሥት ዕቅዶች ናቸው፡፡ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የልማት እንቅስቃሴ የሚደነቅ ቢሆንም በከተሞችም ይሁን በገጠር በመተግበር ላይ ከሚገኙት ግዙፍ ዕቅዶች መካከል በሕዝቡ ላይ በርካታ ሰብዓዊ ቀውሶችን በመፍጠር ላይ የሚገኙ መኖራቸው በግልጽ የሚስተዋል ነው፡፡

ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በመስፋፋት ላይ የሚገኙት በውጭ ባለሀብቶች የተያዙት የእርሻ ፕሮጀክቶችና የመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች (የሸንኮራ አገዳ እርሻው፣ ፋብሪካውና የፋብሪካው ሠራተኞች መኖሪያዎች በራሱ የከተማ ያህል ስፋት እንደሚኖራቸው ልብ ይሏል) በአርሶ አደሮች፣ በከፊል አርሶ አደሮችና አርብቶ አደር ዜጎች ሕልውና ላይ ከባድ አደጋ እያደረሱ ይገኛል፡፡ በተለይም ችግሩን የከፋ የሚያደርገው ለሰፊ የእርሻ ፕሮጀክቶች ከተከለሉ ይዞታዎቻቸው ለሚፈናቀሉ ዜጎች በቂ ካሣና የቀድሞ ሕይወታቸውን ለማስቀጠል አመቺ የሆነ ተለዋጭ ቦታ በመንግሥት በኩል የማይሰጣቸው መሆኑ ነው፤ ይህም ‹‹ልማቱ ዜጎችን ተጠቃሚ ካላደረገ ለማን ነው?›› የሚል ጥያቄ ሲያስነሣ ይደመጣል፡፡ በተለይም በመንግሥት ፍላጎት ብቻ በግዳጅ በሚተገበሩ በመንደር የማሰባሰብና የሠፈራ መርሐ ግብሮች ዜጎችን በአንፃራዊነት አመቺ ከነበሩ የቀድሞ መኖሪያቸው በማፈናቀል ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች እንዲሠፍሩ መደረጋቸውንና ከአዲሱ አኗኗራቸው ጋር ለመላመድ ሲሉም የሚያረቧቸውን ከብቶች ቁጥር ለመቀነስ መገደዳቸውን ‹‹ሒዩማን ራይትስ ዎች››ን የመሳሰሉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋማት የሚያወጧቸው ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የእርሻና የግጦሽ መሬት በነጻ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት እንዳላቸው ቢደነግግም በልማት ስም ይህ መብት እየተጣሰ ዜጎች ሕልውናቸው አደጋ ላይ ሲወድቅ ይስተዋላል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች አንዱና ዋነኛ ባሕርይ የማይነጣጠሉና የማይለያዩ መሆናቸው ነው፡፡ የኢኮኖሚ፣ የባሕልና የማኅበራዊ መብቶቻችን ሳይከበሩልን የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶቻችን ሊከበሩልን አይችሉም፡፡ ይህም የሚያሳየው ሰብዓዊ መብቶች በተግባርም ይሁን በንድፈ ሐሳብ ደረጃ እርስ በርስ ተያያዥና ተደጋጋፊዎች መሆናቸውን ነው፡፡ እርግጥ ነው አንድ ሰው ጦሙን እያደረ ‹‹አማራጮቹን የመወሰን ነጻነት አለው›› ሊባል አይችልም፤ በዚያውም ልክ ግን ጠግቦ የሚያድር ሰው ምርጫዎቹን የመወሰን ነጻነት ሳይኖረው ሲቀር ነገ ጦሙን ላለማደሩ ዋስትና አይኖረውም፡፡ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው በልማት ምክንያት ከነባር ይዞታቸው ተፈናቅለው ሕልውናቸው አደጋ ላይ የወደቀ ዜጎች ንብረት አፍርተው የመጠቀም መብታቸው ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል



## የልማታዊ መንግሥት . . .

በሕይወት የመኖር መብታቸውም እንደተጣሰ ሊቆጠር ይገባል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በ138ኛ ልዩ መግለጫው ይፋ እንዳደረገው በአፋር ክልል በአሳይታና አፋምቦ ወረዳዎች ነዋሪዎች የሆኑ ዜጎች በልማት ስም የእርሻና የግጦሽ መሬታቸውን እንዲለቅቁ በመደረጋቸው በከፍተኛ ችግር ላይ ይገኛሉ፡፡ መሬታቸውን እንዲለቅቁ በክልሉ መንግሥት ቀደም ሲል የተጠየቁ ተጎጂዎች ‹‹ከዱብቲ የተፈናቀሉና የተሰደዱ የአፋር ተወላጆች ከእኛ ጋር አሉ፤ ከእነርሱ ትምህርት ስለወሰድን መሬታችንን ለቅቀን ወደ ሶማሌ ላንድ አንሰደድም፡፡›› የሚል ምላሽ ቢሰጡም የክልሉ መንግሥትና የስኳር ኮርፖሬሽን ከከብት እርባታ እኩል ለአፋር ሕዝብ የሕልውና መሠረት የሆነውን የቴምር ዛፍ ማሳ በቡልዶዘር እንዲጨፈጨፍ አድርገዋል፤ ይህም የሆነው ከነዋሪዎች ስምምነት ውጭ ምንም ዓይነት ካሣ ሳይከፈል ነበር፡፡ እንደተጎጂዎቹ ገለጻ የመንግሥት አካላት የከፊል አርሶ አደሮቹን የቴምር ዛፎች ከመጨፍጨፋቸው በተጨማሪ ለዘመናት የሕልውናቸው መሠረት ሆኖ የቆየውን የአዋሽ ወንዝ ተፈጥሯዊ የፍስሰት አቅጣጫ ማስለወጣቸው ከድርቁ ጋር ተዳምሮ በአካባቢው የከፋ የሰብዓዊ ቀውስ እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡

መሬት ‹‹የሕዝብ እና የመንግስት›› በመሆኑ ምክንያት (በተግባር የገዢው ፓርቲ ቢሆንም) የመንግሥትን የልማት ዕቅዶች ለማስፈጸም ሲባል አርሶ አደሮችና ከፊል አርሶ አደሮች ለሚደርስባቸው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የሚያገኙት የሕግ ከለላ አለ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ በተለይም አሁንም ድረስ ‹‹በኢኮኖሚ ዕድገት ኋላ ቀር›› ተደርገው በሚቆጠሩ አካባቢዎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦች በመንግሥት የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደ አጋር ወይም ባለድርሻ ተደርገው አለመቆጠራቸው ለግጭቶች መንሥዔ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ብዙ ደም ላፋሰሰው የኦሮሚያ ተቃውሞም መንሥዔው መንግሥት ሕዝቡን ባለድርሻ አካል አድርጎ በመውሰድ በልማት ዕቅዶቹ ላይ አለማሳተፉ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

በግብርና ከሚተዳደሩ ዜጎች ዕውቅናና ስምምነት ውጭ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ የእርሻ መሬት ለውጭ ባለሀብቶች የተሰጠበት ኺደት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሐገር ውስጥና ከሐገር ውጭ ከፍተኛ ትኩረት የሳበ የመነጋገሪያ ርእሰ ጉዳይ ነበር፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅና ከእሲያ ለመጡ የውጭ ባለሀብቶች ከ50 እስከ 100 ሺህ ሄክታር የሚደርስ ለም የእርሻ መሬት በዓመት በጣም አነስተኛ በሆነ ገንዘብ በኪራይ ተላልፎ ተሰጥቷል፡፡ ኢኮኖሚያቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የዓለም አገራት መካከል አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በሚከሰት ድርቅና ረኀብ በሕዝቦቿ ላይ ከባድ ጉዳት ሲደርስ መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በተጠቀሰው መልኩ የእርሻ መሬት ወስደው ሰብል የሚያመርቱ የውጭ ባለሀብቶች ምርታቸውን ሰፊ የምግብ ፍላጎት ባለበት የአገር ውስጥ ገበያ አለማቅረባቸው የመንግሥት ፖሊሲን ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ ከትቶታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በልዩ አስተያየት ሰፊ የእርሻ መሬት ከወሰዱ የውጭ ባለሀብቶች ውስጥ የተወሰኑት ጥብቅ የተፈጥሮ ደን በመጨፍጨፍ በሕገ ወጥ የጣውላ ንግድ ላይ መሠማራታቸው ይታወቃል፡፡ እነዚሁ ባለሀብቶች የተረከቡትን መሬት በማልማት ፋንታ ያለሥራ መቀመጣቸው በመጀመሪያ ደረጃ መሬት የማግኘቱ ዕድል ተጠቃሚዎች የሆኑበት ኺደት ለሙስና ተጋላጭ የሆነና ግልጽነት የጎደለው ለመሆኑ አመላካች ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሕግ አውጪውም ሆነ አስፈጻሚ የመንግሥት አካላት ሙሉ በሙሉ በኢሕአዴግ ቁጥጥር ሥር የዋሉ ከመሆናቸው አኳያ በብዙ ቢሊዮን ዶላር ተግባራዊ የሚደረጉ የመንግሥት ሰፊ የልማት ዕቅዶችን አፈጻጸም ሊያጣራ የሚችል ገለልተኛ አካል አለመኖሩ በልማት ስም የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችንና የሙስና ወንጀሎችን አድበስብሶ ለማለፍ አመቺ አድርጎታል፡፡

ስለሆነም፣ በመንግሥትም ይሁን በውጭ ባለሀብቶች ባለቤትነት የተያዙ ግዙፍ የልማት ፕሮጄክቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ተጽዕኖዎች ስለሚኖሯቸው መንግሥት ዜጎችንና የዜጎችን ጥቅም ለማስከበር በተለያዩ መስኮች ላይ የተሠማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በጉዳዩ ላይ ሊያወያይ፤ በውሳኔዎቹም ሊያሳትፍ ይገባል፡፡

ዋቢ ሠነዶች፡-

LAND TO INVESTORS: Large Scale Land Transfers in Ethiopia (Dessalegn Rahmeto, June 2011)

Disconnections and Dilemmas around ‘developmental state’ in Africa (Jan Abbink, July 2015)

# ሰብዓዊ መብት

ሰብዓዊ መብት የሰው ልጅ ነጻነት፣
ቢጫ-ነጭ-ጥቁሩ-በጋራ ‘ሚጋሩት፣
የእግዜር ስጦታ ነው፣
ሰው በመሆን ብቻ እኩል የሚያገኙት።
በተሰጠው ጸጋ ፈጣሪ በደለው፣
አይበላለጥም ዘረ አዳም እኩል ነው።
ወዳለም ሲመጣ-ሲወድቅ ራቁቱን፣
ያን ጊዜ ተሰጠ ክብር ነጻነቱን።
ፍጡር ሆኖ ራሱ ከፍጥረታት በላይ፣
ዓለምን የገራ፣
ዓለምን ያስዋበ፣
በመሬት- በሰማይ፣
እንዴት ባምሳለ ሰው፣
ሲታመስ-ሲቆላ እንየው ሲሰቃይ?
እኩል ሆኖ ሳለ ጥንቱኑ ሲሠራ፣
እንዴት ይዋረዳል፣
እንዴት ሰው ያወጣል ሰውን ከሰው ተራ?
እንደ ግንበኛ ካብ፣
የብረት ድንጋይ ቁስ፣
የፈጣሪ ሕንፃ በሰው እንዴት ይፍረስ?
ልቡ ያሰበውን ወይ ያመነበትን፣
መውጣት በመድፈሩ፣
እንዴት ሰው ይዋረድ፣
እንደምን ይደፈር፣
የሰብዕና ክብሩ?

በ ኃ/ማርያም አማረ